'አሏሁመ‐ህዲኒ ወሰዲድኒ' (ትርጉሙም: አላህ ሆይ ምራኝ፣ አስተካክለኝም።) በልና መመራትን ከአሏህ ስትጠይቅ መንገድን መመራትን አስታውስ። መስተካከልን ስትጠይቅ ደሞ የቀስት ኢላማውን የማግኘት ያህል መገጠምን አስታውስ።

ከዓሊይ (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ: «የአላህ መልክተኛ (ሶለላሁ
ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና እንዲህ አሉኝ: "'አሏሁመ‐ህዲኒ ወሰዲድኒ' (ትርጉሙም: አላህ ሆይ ምራኝ፣ አስተካክለኝም።) በልና መመራትን ከአሏህ ስትጠይቅ መንገድን መመራትን አስታውስ። መስተካከልን ስትጠይቅ ደሞ የቀስት
ኢላማውን የማግኘት ያህል መገጠምን አስታውስ።"» [ሶሒሕ ነው።] [ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ (ሶለላሁ ዐለይሂ ወሰለም) የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና ዓሊይ ቢን አቢ ጣሊብን (ረዲየሏሁ ዐንሁ) - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - አላህን እንዲህ ብሎ እንዲጠይቅና እንዲለምን አዘዙት "አላህ ሆይ! ምራኝ" አቅናኝ፣ ጠቁመኝ "አስተካክለኝ" ግጠመኝ፣ በሁሉም ጉዳዮቼ የተቃና አድርገኝ። ሁዳ (መመራት) ማለት እውነትን በዝርዝርም ሆነ በጥቅሉ ማወቅና እውነትን በግልፅም ሆነ በውስጥ ለመከተል መገጠም ማለት ነው። ሰዳድ "መስተካከል" ማለት: በሁሉም ነገሮች በእውነት ላይ ትክክል በሚሆነው ቀጥ ማለትና መገጠም ማለት ነው። "ሰዳድ" ማለት በንግግርም፣ በተግባርም ሆነ በእምነት ቀጥተኛ የሆነ መንገድ ማለት ነው። ሀሳባዊ ነገር በህዋሳዊ ነገሮች ይብራራሉና አንተ ይህን ዱዓ እያደረግክ "መመራትን ስትማፀን የመንገድ መመራትን" አስታውስ፤ ጉዞ የወጣ ሰው መንገድ መመራት እንደሚጠይቀው መመራት እየጠየቅክ እንደሆነ ቀልብህ ላይ አስቀምጥ። መንገድ የወጣ ሰው ከተመራው መንገድ ከመጥፋት ለመዳን ወደቀኝ ወይም ወደግራ ዘንበል አይልም። ቀጥ ብሎ በመሄዱም ሰላምን ያገኛልም ወደ አላማውም በፍጥነት ይደርሳል። "መስተካከልን ስትጠይቅ ደሞ ቀስት ኢላማውን የማግኘትን ያህል መገጠምን አስታውስ።" አንተ ቀስት ስታነጣጥር በፍጥነት መድረሱንና ኢላማውን ማግኘቱ ላይ ነው የምታተኩረው። ቀስት ወርዋሪ ወደ አንድ ኢላማ ባነጣጠረ ወቅት ቀስቱን ወደ ኢላማው አስተካክሎ ያነጣጥራል። ልክ እንደዚሁ ያሰብከውን መገጠም እንደቀስቱ የተስተካከለ እንዲሆን አድርገህ ነው አላህን የምትጠይቀው። በጥያቄህም የፈለግከው የመመራትን ጥግና የመገጠምን ድካ ይሆናል ማለት ነው። በዚህ ዱዓ ስትማፀን የምትፈልገውን ጉዳይ ቀስት ስትወረውር እንደምታልመው ትክክለኝነት እንዲሆን አላህን መገጠም ስትጠይቅ በቀልብህ ይህን ሀሳብ አስቀምጥ።

https://sunnah.global/hadeeth/am/show/5915